# <u>እንዲህ ነው ዲያስፖራ</u> !

ከ የጆካ

ከራስህ አስበልጠህ ላገር ቅድሚያ ሰጥተህ
ድጋፍህን ልታሰማ ሆ ብለህ ተነስተህ
ምንኛ ደስ ይላል ልብ ብሎ ላየህ።

ከሁሉም  አቅጣጫ ልጆቿ ተጣርተው
አይዞሽ እናት አለም አለሁልሽ ብለው።
በአንድነት ዘመሩ፣ ለቀጣይ መከሩ
እድገቷን አድንቀው ያዩት መሠከሩ።

እንዲህ ነው ዲያስፖራ፣ አገር 'ሚያኮራ
ለኢትዮጵያ እድገት መልካም ታሪክ ሠራ።

ከዛሬ በኋላ . . .
የጥላቻ ፈሊጥ አራማጁ ሁላ
አገርና ህዝብን ሁሌ 'ሚያጥላላ
በተቃዋሚ ስም ኪሱን የሚሞላ።

በቃ! ከእንግዲህ በለው፣ አንቅረህ ትፋው
ቀልድ የለም ባገር ላይ ነቅተናል በለው።

የኢትዮጵያን እድገት ማየት የማይወዱ
በጭፍን ጥላቻ 'ሚያወናብዱ
በሻዕቢያ ቅኝት እስክስታ 'ሚወርዱ።

እነኛን ፅንፈኞች ነቅተናል በላቸው
ማደናገር ትተው ይያዙ ጥጋቸው።